
አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

ቁጥር-15, ጥቅምት 2013 ዓ.ም
Issue No. 15, October 2020

# አዋሽ ዜና መጽሔት
# Awash Newsletter



በማርኬቲንግና ኮምዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የሚታተም
Published by: Marketing & Communication Directorate

8980
contactcenter@awashbank.com
www.awashbank.com

# በዚህ ዕትም


የዋና ስራ አስፈፃሚ መልዕክት....1
አዋሽ ባንክ ´ገበታ ለሀገር´ ፕሮጀክት የብር 30 ሚሊዮን ድጋፍ አደረገ....2
አዋሽ ባንክ ለታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ የብር 25 ሚሊዮን የቦንድ ግዥ ፈፀመ....3
የ8ኛው ዙር ´´ከአዋሽ ይቀበሉ ይሸለሙ!´´ የሎተሪ መርሐ-ግብር ባለዕድለኞች ሽልማታቸውን ተረከቡ....4
አዋሽ ባንክ የሴቶች የቁጠባ ባህልን ለማጠናከር በትኩረት እየሰራ ነው....5
አዋሽ ባንክ ለጎዳና ተዳዳሪዎች እና ለአቅመ ደካሞች የምገባ መርሐ-ግብር የሚውል የገንዘብ ድጋፍ አደረገ....8
አዋሽ ባንክ እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ 50 ሺህ ችግኞችን በመትከል አረንጓዴ አሻራቸውን አኖሩ....9
አዋሽን የሆነው ማነው....17


# In This Issue


Awash Bank launches PayPal Service....11
Articles....12
Proverbs & Quotes....16



**ዋና አዘጋጅ**
ተሾመ ዋቅጅራ
**ረዳት አዘጋጆች**
ድሪባ መገርሳ
ሰላም ተክለጽዮን

**ፎቶግራፍ**
ዳንኤል ምትኩ

**ግራፊክ ዲዛይነር**
ቱሪ እስማኤል

**EDITOR-IN-CHIEF**
Teshome Wakjera

**ASSISTANT EDITORS**
Deriba Megerssa
Selam Tekletsion

**PHOTOGRAPHER**
Daniel Mitiku

**GRAPHIC DESIGNER**
Turi Ismael

# የአዋሽ ባንክ ዋና ሥራ አስፈፃሚ መልዕክት



አቶ ፀሐይ ሽፈራው
የአዋሽ ባንክ ዋና ሥራ አስፈፃሚ

ከሁሉ አስቀድሜ የባንካችን ሠራተኞችና የማኔጅመንት አባላት በተጠናቀቀው 2019/20 የሂሳብ አመት ባንካችን ከታክስና ከሌሎች ተቀናሾች በፊት የብር 4.19 ቢሊዮን ትርፍ በማግኘትና በድጋሚ ከሌሎች ተወዳዳሪ ባንኮች የላቀ ውጤት በማስመዝገብ የተለመደውን የመሪነት ስፍራውን በአስተማማኝ መልኩ እንዲያስቀጥል ከፍተኛ ሚና ያበረከታችሁት ውድ ሠራተኞቻችን ምስጋና ይገባቸዋል።

ባንካችን የተለያዩ ውስጣዊና ውጪያዊ ተግዳሮቶችና ተጽኖዎችን በመቋቋም እንዲሁም በሀገራችን የተከሰተውን የኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ወረርሽኝ በሽታ በመከላከልና ብርቱ ጥረት በማድረግ ላስመዘገባቸው ስኬቶች እንደምክንያት ከሚጠቀሱት ስትራቴጂዎች ውስጥ በዋናነት :-

- የባንካችን የዳይሬክተሮች ቦርድ፣ ማኔጅመንት እና ሠራተኞች በባንኩ የ10 አመት ፍኖተ ካርታ ላይ የተቀመጡትን አላማዎችና ግቦችን ለማሣካት በአንድ ልቦናና ሃሣብ ተባብረው መሥራት፣

- የቅርንጫፎቻችንን ብዛት በማሳደግ እንዲሁም ከ716,000 በላይ አዳዲስ ደንበኞችን ከማፍራት ባሻገር ትላልቅ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና የግል ተቋማትን የባንኩ ደንበኞች በማድረግና አዳዲስ የኤቲኤም፣ የሞባይል ባንኪንግ እና የኢንተርኔት ባንኪንግ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣

- የዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎቶችን የተለያዩ የክፍያ አገልግሎቶች አማራጭ እንዲኖሩት በማድረግ ተገልጋዩ ህብረተሰብ የሞባይል ስልኮች የአየር ሰዓት ግዢ፣ የአውሮፕላን ቲኬት ግዢ፣ የትምህርት ቤት፣ የስልክ፣ የዲኤስቲቪ እና የዋይ ፋይ የአገልግሎት ክፍያዎችን በሞባይል ባንኪንግ የሚፈፅሙበትን ምቹ አገልግሎት መስጠት እንዲሁም የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ማሳደግ በዋናነት ይገኙበታል።

ይህ ባንካችን ያስመዘገበው የላቀ ውጤት የሁሉም ሠራተኞች የጋራ ጥረት መሆኑን ለዳይሬክተሮች ቦርድ በማስረዳት በተደረሰው የውሳኔ አቅጣጫ መሰረት ለእያንዳንዱ ሠራተኛ የሶስት ወር ማትጊያ ደሞዝ ከመፈቀዱም ባሻገር የደሞዝ ማስተካከያ መደረጉ የሚዘነጋ አይደለም፣ በዚህም እንኳን ደስ አለን ! እንኳን ደስ አላችሁ ለማለት እወዳለሁ።

ውድ የባንካችን ቤተሰቦች ያለንበት የፋክክር ወቅት እንደመሆኑ የሚገጥሙንን ውጫዊ ችግሮች ወደ መልካም አጋጣሚ በመቀየር በመጭውም የሂሳብ ዓመት የተለመደውን የስራ ባህላችንን በማጠናከር በአዲስ ሞራልና ተነሳሽነት እራሳችንን ከኮሮና ወረርሽኝ በሽታ እየጠበቅን እንዲሁም ግዜያችንን በአግባቡ በመጠቀም ስራችንን እንድንከውን ከአደራ ጭምር እያሳበብኩ አዲሱ አመት የሰላም፣ የጤና እንዲሁም የዕድገት እንዲሆንልን መልካም ምኞቴን ለመግለጽ እወዳለሁ ! አመሰግናለሁ።

# አዋሽ ባንክ ‘ገበታ ለሀገር’ ፕሮጀክት የብር 30 ሚሊዮን ድጋፍ አደረገ




የአዋሽ ባንክ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ፀሐይ ሽፈራው ጋዜጣዊ መግለጫ በሰጡበት ወቅት

አዋሽ ባንክ ምንም እንኳን ለትርፍ የተቋቋመ የግል የፋይናንስ ተቋም ቢሆንም አገራዊ ማህበራዊ ግዴታውን ከመወጣት አኳያ ለቱሪስት መዳረሻ ስፍራዎች ግንባታ የሚውልና ‘ገበታ ለሀገር’ የተባለውን ፕሮጀክት ለመደገፍ የብር 30 ሚሊዮን ድጋፍ አድርጓል።

ባንኩ በዘንድሮ ዓመት በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይፋ የተደረገውና በኦሮሚያ በወንጪ ሐይቅ፣ በአማራ በጎርጎራ እና በደቡብ ክልል በኮይሻ ለመስራት ለተቀረፀው የገበታ ለአገር ፕሮጀክት ለእያንዳንዳቸው የብር 10 ሚሊዮን በድምሩ የብር 30 ሚሊዮን የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ ችሏል።
መንግስት ለሚቀርፃቸው የተለያዩ የልማት ፕሮጀክቶች በግንባር ቀደምትነት ፋይናንስ ድጋፍ በማድረግ የሚታወቀው አዋሽ ባንክ በአሁኑ ወቅት በመጠናቀቅ ላይ ላለው የሸገር ማስዋብ ፕሮጀክትም የብር 15 ሚሊዮን የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ አሻራውን አኑሯል።

በተመሳሳይ ሁኔታ ባለፈው ዓመት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተቀርፆ ተግባራዊ ለሆነው ለተማሪዎች የመማሪያ ቁሳቁሶችን የማሟላት ስራን በሰፊው የደገፈ ሲሆን  ዘንድሮም ለተማሪዎች ምገባ ፕሮግራምና ለትምህርት ግብዓቶች ማሟያ የብር ሶስት ሚሊየን የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል።

አዋሽ ባንክ በዘርፉ ፈር ቀዳጅ እንደመሆኑ መጠን የአገሪቱ የፋይናንስ ህጎችን አክብሮና በየጊዜው በብሔራዊ ባንክ የሚወጡ መመሪያዎችን በአግባቡ በመተግበር ላለፉት 26 ዓመታት በስኬት ጎዳና ላይ ያለና በሁሉም የዘርፉ መመዘኛዎች በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ መሪ የግል ባንክ ሲሆን በ2012 የበጀት ዓመት ከብር 1.3 ቢሊዮን በላይ  የመንግስት ግብር በመክፈል ከከፍተኛ የግብር ከፋይ ኩባንያዎች አንዱ በመሆን በፕላቲኒየም ደረጃ በኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ መሸለሙ ይታወሳል።

በሌላ በኩል አዋሽ ባንክ የብር ኖት ለውጡን ተከትሎ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመርያ መሠረት የአዳዲሶቹ የብር ኖቶች ቅያሪ ከመስከረም 6 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ አበባ እና በተለያዩ ክልል ከተሞች አገልግሎቱን በመስጠት የመጀመርያው የግል ባንክ ከመሆኑም ባሻገር ከብሔራዊ ባንክ የተረከበውን አዳዲስ የብር ኖቶችን ለሌሎች የግል ባንኮች በማሰራጨት ረገድ በአዲስ አበባ፣ በአዳማ፣ በሐረር፣ በሻሸመኔ፣ በጅማና በነቀመቴ ከተሞች ባሉት ስድስት issue ቅርንጫፎቹ በመታገዝ አገልግሎቱን በአጭር ጊዜ ውስጥ እና በአስተማማኝ ሁኔታ ሊያዳርስ ችሏል።

# አዋሽ ባንክ ለታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ የብር 25 ሚሊዮን የቦንድ ግዥ ፈፀመ




የታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ቦንድ ግዥ የቼክ ርክክብ ሥነ-ሥርዓት

ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ቦንድ በመግዛትና ገንዘብ በመለገስ አስፈላጊውን የፋይናንስ ድጋፍ እያደረጉ ይገኛል፡፡

አዋሽ ባንክም ለግድቡ ግንባታ የብር 25 ሚሊዮን የቦንድ ግዥ ፈፅሟል፡፡ የአዋሽ ባንክ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ፀሐይ ሽፈራው ቦንዱ የተገዛበትን ቼክ ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ም/ቤት ጽ/ቤት ባስረከቡበት ወቅት እንደገለፁት ታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ለሀገሪቱ ሁለንተናዊ እድገት ትልቅ ፋይዳ የሚኖረው በመሆኑ አዋሽ ባንክም የበኩሉን አሻራ በማሳረፍ ላይ ይገኛል፡፡

በቦንድ ርክክብ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ የተገኙት የታላቁ ህዳሴ ግድብ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ምክር ቤት ጽ/ቤት ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ ሮማን ገብረ ስላሴ በበኩላቸው የቦንድ ግዥው የግድቡን ግንባታ ከማገዙም ባሻገር የፋይናንስ ተቋማትንም ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ገልፀዋል፡፡

የግድቡን የመጀመርያ ዙር ውሃ ሙሌት መጠናቀቅ ተከትሎ የህብተረተሰቡ ተሳትፎ እያደገ በመምጣቱ በሐምሌ ወር ብቻ ከ 116.5 ሚሊዮን ብር በላይ መሰብሰብ መቻሉን የጠቆሙት ዋና ዳይሬክተሯ አዋሽ ባንክ ላደረገው የቦንድ ግዥ በማመስገን አርአያነቱን ሌሎችም ሊከተሉት ይገባል ብለዋል፡፡

አዋሽ ባንክ ያደረገውን የ25 ሚሊዮን ብር የቦንድ ግዥን ጨምሮ በተለያዩ ግዜያት የተለያዩ ድጋፎችን ሲያደርግ መቆየቱንና በቀጣይም የግድቡ ግንባታ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ድጋፉን አጠናክሮ እንደሚቀጥል አቶ ፀሀይ ሽፈራው በአፅኖት ገልፀዋል፡፡

# የ8ኛው ዙር ‘’ከአዋሽ ይቀበሉ ይሸለሙ!’’ የሎተሪ መርሐ-ግብር ባለዕድለኞች ሽልማታቸውን ተረከቡ



አቶ አብደላ ቃሲም  የ1ኛ ዕጣ ዘመናዊ የጭነት መኪና አሸናፊ ቁልፍ ሲረከቡ

ባንካችን ተግባሩ ልክ እንደ መሪ ቃሉ የደንበኞቹን ፍላጎት ማርካት እንደመሆኑ መጠን የገባውን ቃል በማክበር የስምንተኛውን ዙር “ከአዋሽ ይቀበሉ ያሸንፉ” መርሐ ግብር ከታህሳስ 20 ቀን 2012 ዓ.ም እስከ ግንቦት 19 ቀን 2012 ዓ.ም ድረስ ሲያካሂድ ቆይቷል። የስምንተኛው ዙር “ከአዋሽ ይቀበሉ ያሸንፉ” የውጭ ምንዛሪ ማስገኛ የሎተሪ መርሐ ግብር ልክ እንዳለፋት ሰባት ዙሮች በተሳካ ሁኔታ ተጠናቆ ዕጣው ሐምሌ 21 ቀን 2012 ዓ.ም በብሔራዊ ሎተሪ አዳራሽ በይፋ ወጥቷል።

ለመርሐ-ግብሩ የተዘጋጁት የሽልማት ዓይነቶች በሶስት ደረጃዎች የተከፋፈሉ ሲሆኑ ለአንደኛው ዕጣ የተዘጋጀው የሽልማት ዓይነት ብር 1.6  ሚሊዮን የሚያወጣ አንድ ዘመናዊ አይሱዙ የጭነት መኪና ለሁለተኛ ዕጣ (አራት ዕጣዎች) እያንዳንዳቸው 32 ኢንች ኤልኢዲ ቴሌቪዥኖች እና ለሶስተኛ ዕጣ (አምስት ዕጣዎች) እያንዳንዳቸው ዘመናዊ የውሃ ማጣሪያ እንዲሁም አራተኛ ዕጣ (ሃያ ዕጣዎች) እያንዳንዳቸው ስማርት የሞባይል ስልክ ቀፎዎች  ናቸው።

የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ባወጣው ዕጣ መሰረትም ብር 1.6 ሚሊዮን የሚያወጣው ዘመናዊ አይሱዙ የጭነት መኪና የሎተሪ ቁጥር 055781 የያዙት አቶ አብደላ ቃሲም አብዩ ከዶዶላ ከተማ (ዶዶላ ቅርንጫፋችን) የተላከላቸውን የውጭ ምንዛሪ ተቀብለው አሸናፊ ሆነዋል።

በተመሳሳይ መልኩ ሌሎች በርካታ ለሎተሪ ዕጣው የተዘጋጁ ሽልማቶችም ለዕድለኞች ደርሰዋል።

የአዋሽ ባንክ የ8ተኛ ዙር ከአዋሽ ይቀበሉ ይሸለሙ የሎተሪ ፕሮግራም አጠናቆ አሸናፊ ለሆኑት ዕድለኞች ያዘጋጀዉን ሽልማት አስረክቧል።

በ8ኛው ዙር ከአዋሽ ይቀበሉ ይሸለሙ የሎተሪ መርሀ-ግብር በ1ኛ ዕጣ ዘመናዊ አይሱዙ የጭነት መኪና አሸናፊ የሆኑት አቶ አብደላ ቃሲም በቀን ሠራተኝነት የሚተዳደሩ ሲሆን የመኪናውን ቁልፍ በተረከቡበት ወቅት እንደገለጹት ዕድለኛ በመሆናቸው

ወደሚቀጥለው ገጽ ተዘዋውሯል......

የተሰማቸውን ከፍተኛ ደስታ ገልጸው ''አጋጣሚው ህይወቴን ወደ አዲስ ምዕራፍ ያሸጋገረ ነው'' ብለዋል።

ባንካችን እስካሁን ባዘጋጀው የውጭ ምንዛሪ ማስገኛ የሎተሪ መርሐ-ግብር መኪና የሚያስገኝ 1ኛ ዕጣ አሸናፊ የሆኑት በመምህርነት፣ በልብስ ሰፊት፣ በግብርና፣ በፖሊስነት፣ በቀን ሠራተኝነትና በትናንሽ ንግዶች ላይ የተሰማሩ ሰዎች መሆናቸው አይዘነጋም።

ባንካችን ከአዋሽ ይቀበሉ፤ ያሸንፉ የሎተሪ ዕጣ መርሀ-ግብር ሲያዘጋጅ ሶስት ዋና ዋና ዓላማዎችን ታሳቢ በማድረግ ሲሆን የመጀመሪያው ለአገራችን የኢኮኖሚ ዕድገት በጣም አስፈላጊ እና ወሳኝ የሆነውን የውጭ ምንዛሪ ፍሰት እንዲጨምር ማድረግ ነው።

ሁለተኛው ዓላማ በህገ-ወጥ መንገድ ወደ አገራችን የሚመጣውን የውጭ ምንዛሪ በሕጋዊ መንገድ እንዲመጣ ለማድረግና የሚገኘውንም የውጭ ምንዛሪ ለአገራችን ልማትና ዕድገት እንዲውል ለማስቻል ሲሆን ሦስተኛው ዓላማችን ደግሞ ከተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች የተላከላቸውን የውጭ አገር ገንዘቦች በአዋሽ ባንክ በኩል የሚቀበሉ ወይም አምጥተው የሚመነዝሩ ደንበኞቻችን በሽልማት መልክ ማበረታቻ እንዲያገኙ ማድረግ መሆኑ ተጠቃሽ ነው።

ከዚህ አኳያ ላለፉት ስምንት ተከታታይ ዙሮች የተካሄደው የሎተሪ ማበረታቻ ሥነ-ሥርዓት በአብዛኛው የተቀመጠላቸውን ግቦች ማሳካት ችለዋል።

# አዋሽ ባንክ የሴቶች የቁጠባ ባህልን ለማጠናከር በትኩረት እየሰራ ነው

ሴቶች ለአንድ ሀገር እድገትና ህልውና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያበረክቱት አስተዋፆኦ ቀላል የሚባል ባይሆንም ላለፉት በርካታ ዓመታት የሴቶች ማህበራዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ በተለያዩ ጫናዎች የተነሳ አነስተኛ እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም።
ይህን እንጂ በአሁኑ ወቅት በርካታ ሴቶች የሚያጋጥማቸውን ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ተግዳሮቶች ከመቋቋማቸውም ባሻገር ከመሪነት ጀምሮ በተለያዩ ሀገራዊም ሆነ አለም አቀፍ መድረኮች ላይ የአንበሳውን ድርሻ እየተወጡ ይገኛሉ።

አዋሽ ባንክ ይህን የሴቶች ተሳትፎ ይበልጥ በማጠናከርና የፋይናንስ አቅማቸውን በማሳደግ እንዲሁም ከጥገኝነት በማላቀቅ የወደፊት ራዕያቸውን ለማሳካት እንዲያግዛቸው በማሰብ ሉሲ የተሰኘ ልዩ የሴቶች የቁጠባ ሂሳብ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል።

'ሉሲ' ልዩ የሴቶች የቁጠባ ሂሳብ እድሜአቸው ከ18 ዓመት በላይ ለሆኑ እና በሁሉም የኢኮኖሚ ደረጃ ላሉ ሴቶች የገንዘብ እንቅስቃሴ በማቀላጠፍ የወደፊት ህይወታቸው ብሩህ ለማድረግ ታሳቢ ሆኖ የተዘጋጀ ሲሆን ከሌሎች የቁጠባ ሂሳብ አይነቶች ለየት የሚያደርገው ሴቶች ራሳቸው በሚያንቀሳቅሱት ተቀማጭ ሂሳብ ጠቀም ያለ ወለድ እንዲያገኙ ምቹ እድል ይፈጥርላቸዋል።

አዋሽ ባንክ የጀመረው ይህ ልዩ የሴቶች የቁጠባ ሂሳብ አገልግሎት ለታለመለት አላማ እንዲውል በሁሉም ቅርንጫፎች በርካታ ስራዎች እየተከናወኑ ሲሆን በቀጣይ ግዜያትም የአገልግሎቱ መስፋፋት በባንኩ የተቀማጭ ሂሳብ እድገት ላይ ከፍተኛ አስተዋፆኦ እንደሚኖረው ይታመናል።

ስለአገልግሎቱ አሰጣጥና ጠቀሜታዎች ግንዛቤ ለማስጨበጥ የሚረዱ የተለያዩ የማስታወቅያ ቁሳቁሶች በዋናው መ/ቤት የገበያ ጥናት ዳይሬክቶሬት ተሰርተው ወደ ሁሉም ቅርንጫፎች ከመሰራጨታቸውም ባሻገር የሬድዮና የቴሌቪዥን ማስታወቅያዎችም በተለያዩ ቋንቋዎች ተሰርተው አገልግሎቱን የማስተዋወቅ ሥራ በሰፊው እየተሰራ ይገኛል።

ሉሲ
Lucy



ልዩ የሴቶች
የቁጠባ ሒሳብ

በስኬቴ ሁሉ...

አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

# ለክቡራን ደንበኞቻችን በሙሉ!

## በባንካችን የደንበኞች አገልግሎት መስመር

# 8980

## ላይ በመደወል በማንኛዉም ጊዜ እና ሰዓት

## ጥያቄ፣አስተያየት እና ቅሬታዎን ማቅረብ ይችላሉ!




P.O.Box: 12638 contactcenter@awashbank.com

# አዋሽ ባንክ ለጎዳና ተዳዳሪዎች እና ለአቅመ ደካሞች የምገባ መርሐ-ግብር የሚውል የብር 200 ሺህ የገንዘብ ድጋፍ አደረገ፡፡





የ4ኛው ዙር የመዓድ ማጋራት ሥነ-ሥርዓት

አዋሽ ባንክ የኢፌድሪ ስፖርት ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፣ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን እንዲሁም ሌሎች አጋር ድርጅቶች በጋራ በመሆን በአዲስ አበባ ትንሿ ስታዲየም ነሀሴ 2 ቀን 2012 ዓ.ም ላስጀመሩት 4ኛው ዙር የምገባ ፕሮግራም የብር 200 ሺህ ድጋፍ አደረገ ።

የምገባ ፕሮግራሙ ቀደም ሲል ሲካሄድ የቆየው የኮሮና ቫይረስ ስርጭትን በጋራ ለማሸነፍ የኢፌድሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር አብይ አህመድ (ዶ/ር) የማዕድ ማጋራት ብሔራዊ ጥሪ ተከትሎ ሲሆን አዋሽ ባንክን ጨምሮ የተለያዩ ለጋሽ ድርጅቶች እና ባለሃብቶች ባደረጉት ድጋፍ የምገባ ፕሮግራሙ ለ4ኛ ወር ሊቀጥል ችሏል ።

በፕሮግራሙ ላይ በመገኘት ንግግር ያደረጉት የኢፌድሪ ስፖርት ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር ክቡር አቶ ዱቤ ጅሎ የኮሮና ቫይረስ ከተከሰተ ጀምሮ ኮሚሽኑ የተለያዩ ማህበራዊ ኃላፊነቶችን እየተወጣ መሆኑን ጠቁመው ፲ይህ የምገባ ፕሮግራምም በተሳካ ሁኔታ እንዲካሄድ አዋሽ ባንክ ላደረገው የገንዘብ ድጋፍ ከፍተኛ ምስጋና አቅርበዋል።

እስካሁን በተደረገው የምገባ ሂደት እነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች የዕለት ምግብ እንዲያገኙ ከማድረግ ባሻገር ለወረርሽኙ ያላቸው ተጋላጭነት እንዲቀንስና የተወሰኑት ቋሚ ድጋፍ እንዲያገኑ መደረጉንም ም/ኮሚሽነሩ ገልጸዋል።

በሌላ በኩል መስከረም 17 ቀን 2013 ዓ.ም በተካሄደው የማዕድ ማጋራት የማጠቃለያ መርሀ-ግብር ላይ ባንኩ ላደረገው የፋይናንስ ድጋፍ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ተ/ፕሬዚዳንት ክብርት ደራርቱ ቱሉ እውቅናና የምስጋና ምስክር ወረቀት አበርክተዋል ።

አዋሽ ባንክ ከምስረታው ጀምሮ የፋይናንስ አገልግሎቱን ተደራሽ ከማድረጉም ባሻገር የማህበረሰቡን ችግር በመረዳት እገዛና ድጋፍ በማድረግ ላይ ሲሆን በተለይ የኮሮና ቫይረስ በሃገራችን ከተከሰተ ግዜ ጀምሮ ማህበራዊ ሃላፊነቱን በሚገባ በመወጣት ላይ እንደሚገኝና በቀጣይም በሚደረጉ በጎ ተግባሮች ላይ ከመንግስት ጎን በመቆም ጉልህ ድርሻ እንደሚጫወት በመርሐ-ግብሩ ላይ ተጠቁሟል።

# አዋሽ ባንክ እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ 50 ሺህ ችግኞችን በመትከል አረንጓዴ አሻራቸውን አኖሩ

እህት ኩባንያዎቹ አዋሽ ባንክ እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ ሐምሌ 25 ቀን 2012 ዓ.ም በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን በሰበታ ሐዋስ ወረዳ በደበል ዮሐንስ ተራራ ከወረዳው የእርሻና የተፈጥሮ ሀብት ፅ/ቤት ጋር በመተባበር 20 ሺህ ችግኞችን በመትከል አረንጓዴ አሻራቸውን አኑረዋል።

የአዋሽ ባንክ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ፀሐይ ሽፈራው በፕሮግራሙ ላይ ባደረጉት ንግግር እህት ኩባንያዎቹ አዋሽ ባንክና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ ባለፉት 26 ዓመታት ውስጥ በሀገራችን የልማትና የምጣኔ ሀብት ዕድገት ውስጥ አሻራቸውን ካስቀመጡት የግል የፋይናንስ ተቋማት መካከል ግንባር ቀደም ከመሆናቸውም በተጨማሪ ለአገሪቱ የአረንጓዴ አሻራ መርሐ-ግብርም ትልቅ ተሳትፎ ሲያደርጉ የቆዩና አሁንም እያደረጉ ያሉ ናቸው ብለዋል።



የአዋሽ ባንክ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ፀሐይ ሽፈራው በችግኝ ተከላ መርሐ-ግብሩ ላይ ንግግር ሲያደርጉ

የጠቅላይ ሚኒስትራችንን የአረንጓዴ አሻራ ጥሪ በመቀበልና 25ኛ ዓመት የምስረታ በዓላቸውን ምክንያት በማድረግ ሐምሌ 13 ቀን 2011 ዓ.ም በእንጦጦ ተራራ እህት ኩባንያዎቹ አስር ሺህ ችግኞችን በመትከል አሻራቸውን  አኑረዋል፣ ያሉት አቶ ፀሐይ በዚህ ረገድ እህት ኩባንያዎቹ የቆየ ልምድ እንዳላቸውም ጠቁመዋል። ከዚህ በፊት በተለያዩ አካባቢዎች የተከሏቸውና በዚህ ዘርፍ ላይ ለተሰማሩት አካላት ባደረጉት ድጋፍ የተተከሉ ችግኞች ዛሬ ላይ ወደ ደንነት ተለውጠው የአከባቢውን የተፈጥሮ ሚዛን ከማስጠበቅ አንፃር ጉልህ አስተዋፅኦ እያበረከቱ መሆኑንም በአብነት ጠቅሰዋል።

ባለፈው ዓመት ከኢትዮጵያ ተፈጥሮና የቅርስ ጥበቃ ባለአደራ ማህበር ጋር በመተባበር በእንጦጦ ተራራ የተተከሉ ችግኞችም እህት ኩባንያዎቹ ለጥበቃና እንክብካቤያቸው በቂ በጀት በመመደባቸው ከ70 በመቶ በላይ ፀድቀው በአሁኑ ሰዓት በጥሩ ሁኔታ ላይ እንደሚገኙም  ገልፀዋል።



በዘንድሮ ዓመትም ባለፈው ዓመት “አንድ ሰው አርባ ችግኝ በሚል” በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተጀመረውን የአረንጓዴ አሻራ መርሐ-ግብር ለማስቀጠል እህት ኩባንያዎቹ “የአዋሾች የአረንጓዴ አሻራ ቀን” በሚል መሪ ቃል በጋራ በመሆን በአገር አቀፍ ደረጃ እስከ 50 ሺህ የሚደርሱ ችግኞችን ይተክላሉ ያሉት ዋና ስራ አስፈፃሚው ከእነዚህም ውስጥ ከሰበታ ሐዋስ እርሻና የተፈጥሮ ሀብት ፅ/ቤት ጋር በመተባበር በሁለት ሄክታር መሬት ላይ የሚተከሉ ሃያ ሺህ ችግኞች የዘመቻው ዋነኛው አካል መሆኑን አስረድተዋል። በሁሉም የአገራችን ክፍሎች የሚገኙ የቀጠና ፅ/ቤቶችና የቅርንጫፍ ሠራተኞቻችንም ባሉበት አካባቢ ካሉት የመንግስት መዋቅሮች ጋር በመቀናጀትና ሠራተኞቻቸውን በማስተባበር ሰላሳ ሺህ ችግኞችን እንደሚተክሉም አስታውቀዋል።

የዘንድሮውን የችግኝ ተከላ ከሌላው ጊዜ ለየት የሚያደርገው ለእህት ኩባንያዎቻችን ስያሜ መነሻ የሆነውና የአገራቸን የልማት አጋር በሆነው የአዋሽ ወንዝ ተፋሰስ ላይ የሚካሄድ እንደመሆኑ መጠን ለአዋሽ ወንዛችን የሚደረገው ጥበቃ አካል ተደርጎ ሊታይ የሚችል መሆኑንም አቶ ፀሐይ ጠቁመዋል። ከዚህም በተጨማሪ በችግኝ ተከላ መርሐ-ግብር በጉድጓድ ዝግጅት፣ በተከላና በቀጣይነት በሚሰራው የጥበቃና እንክብካቤ ስራ ለአከባቢው ወጣቶች የስራ ዕድል እና በወረዳው በችግኝ አምራችነትና ሽያጭ ለተደራጁ ወጣቶችም የገበያ ዕድል ለመፍጠር መቻሉንም ገልፀዋል።

የአዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ጉዲሳ ለገሰ በበኩላቸው የ2012 ዓ.ም የችግኝ ተከላ ፕሮግራም ዓላማ እህት ኩባንያዎቹ አዋሽ ባንክና አዋሽ ኢንሹራንስ ከአካባቢ ጥበቃ አንፃር ያለባቸውን ተቋማዊ ማህበራዊ ኃላፊነት በመወጣት በደኖች መመናመን አማካይነት ሊመጣ የሚችለውን የአየር ንብረት ለውጥና ተጓዳኝ ችግሮችን ከመቋቋም አንፃር ለተነደፈው አገራዊ ፖሊሲ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ለማበርከት መሆኑን አስረድተዋል።



የአዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ጉዲሳ ለገሰ በችግኝ ተከላ መርሐ-ግብሩ ላይ ንግግር ሲያደርጉ

የአካባቢው ህብረተሰብም ይህንኑ ተረድቶ ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ እንዲያደርግ በማሳሰብ እህት ኩባንያዎቹ ለተከሏቸው ችግኞች አስፈላጊውን በጀት በመመደብ ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ እያደረጉላቸው በተፈለገው መልኩ አድገው የአካባቢያችንና የአገራችንን ተፈጥሯዊ ሚዛን በማስጠበቅ ውስጥ ድርሻ እንዲኖራቸው እንደሚያደርጉም አቶ ጉዲሳ አረጋግጠዋል።

# Awash Bank Launches PayPal Service

PayPal is a digital payment service that customers can use while shopping online. PayPal stores payment info, such as bank account or credit card numbers, so that customers don't have to type out the numbers every time they buy something.

Awash Bank is pleased to announce that it is launching the PayPal service for the first time in our country by working with the world-renowned that most efficient payment system in the world. PayPal service that intended a customer to accept incoming money transfers from abroad via an international Money transfer PayPal and also incorporate payments into their online checkout process.

As a PayPal member, you can:

- Get a cash advance from your credit card and deposit the amount in your PayPal account.
- Make person-to-person (P2P) payments by transferring money from your PayPal account to another.
- Have a check mailed to you for the balance of your PayPal account.
- Get a PayPal debit card that you can use to make real-world purchases from your PayPal account.

To use PayPal, both sellers and buyers must sign up for a PayPal account. This process will include linking a bank account or a credit card. It's a fairly quick process, and once it's set up, you're ready to use PayPal.

PayPal uses encryption to keep your financial information secure.

It also offers fraud prevention, which seeks to recognize and block fraudulent charges, as well as purchase protection, which reimburses customers whose purchase never arrives in the mail.

# Top Growth Segments: Global ATM Market (2016 - 2022) - Expected to Grow 8.5% - Research and Markets

An Automatic Teller Machine (ATM) is a machine which enable people to withdraw cash from individual bank accounts. Introduced in the developed countries during the late 1970s, ATM machines were considered to be nothing more than cash dispensers, which customers could use to withdraw cash and receive details of their bank accounts.

The global ATM market, in the developing countries has been progressively growing, while indicating an evolved life cycle in the developed countries. Rising demand for automated system, growth of ATM industry in emerging markets, better security standards, technological advancements, and introduction of wireless communicating devices, etc are some of the leading market driving factors for the growth of the ATM market globally. On the other hand, the rising incidences of ATM card skimming and hacking customers' personal and bank account information would act as the major restraining factors associated with the ATM market.

In 2015, Mobile ATM grew with the highest growth rate for period 2012 - 2015. The segment has registered revenue of USD 879.7 million in 2015. The Worksite segment is expected to attain a market size of USD 2,890.2 million by 2022 experiencing a high growth rate during the forecast period.

Further, in terms of ATM types, the White label ATMs, Smart ATMs market segment are expected to grow at the high growth rates thereby offering huge business opportunities as compared to the other ATM types including conventional bank ATMs, brown label ATMs and cash dispenser ATMs. (Source:- https:/www.businesswire.com)

# The World's Best Banks: The Future Of Banking Is Digital After Coronavirus

When Citigroup opened 2020, the most ambitious projects at the $2.2 trillion in assets lender involved major partnerships with technology companies best known for their internet, social media and ecommerce platforms.

In China, nearly 70% of the payments that Citigroup handles for customers are done through AliPay, the payments business spawned by Alibaba. Citigroup's digital payments technologies are also present on other popular social messaging platforms like LINE and WeChat. The mega-lender recently launched a credit card partnership with fintech Paytm in India and in Singapore it uses chatbots on Facebook Messenger to help answer customer service inquiries. In November 2019, the bank made a big splash in the United States by unveiling a digital checking account with Google Pay.

These partnerships are part of a new reality for the banking industry's most important players like Citigroup: Innovative and seamless digital banking capabilities are paramount in a business where basic financial products have become commoditized and rock-bottom interest rates make it hard for lenders to differentiate. Consumers are instead voting with their smartphones, demanding the ability to conduct their financial activities safely and easily on mobile phones and their desktops.

Never were these growing demands more important than during the coronavirus pandemic, which forced countries around the world to announce lockdowns to combat the spread of the virus. Unable to visit bank branches, consumers turned to mobile apps and online services to get transactions done.

In the U.S. Citi saw an 84% increase in daily mobile check deposits in May and a tenfold surge in activity on Apple Pay as quarantined customers used digital and contact-less tools to handle their financial activities. The lender's Mexican operations saw an 80% increase in mobile app logins in March. Downloads of its mobile app surged 116% from February to April, while digital bill payments rose 78%.

"Banking has changed irrevocably as a result of the pandemic. The pivot to digital has been supercharged," says Jane Fraser, president of Citigroup and CEO of its gigantic consumer bank. He also add "We believe we have the model of the future – a light branch footprint, seamless digital capabilities and a network of partners that expand our reach to hundreds of millions of customers."

Forbes partnered with market research firm Statista to measure the best banks in nearly two dozen countries. Statista surveyed more than 40,000 customers around the globe

for their opinions on their current and former banking relationships. The banks were rated on overall recommendation and satisfaction, as well as five subdimensions (trust, terms and conditions, customer services, digital services and financial advice). Between 5 and 75 banks were identified as top banks in each country, based on the total evaluations collected, the number of banks in the specific country and the scores achieved.

The 2008 financial crisis didn't just usher in an era of consolidation and low rates that reshaped the banking industry globally, it also coincided with the mass adoption of the smartphone and a shift to digital banking. In the wake, a crop of web-first lenders emerged to challenge the world's biggest banks and made offering end-to-end mobile banking features a matter of survival. The coronavirus only affirmed that there's no looking back.

Now, with Covid-19 affirming most digital banking trends, Bogdaneris wonders whether ING will increase the digital banking pace. Says Bogdaneris, "Where we have physical distribution and literally closed branches, the question is when the Covid-19 crisis abates - are some of them still needed? (Source:-https://www.forbes.com )

አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

# ኮሮና ቫይረስን በጋራ እንከላከል!!

## የበሽታው ምልክቶች | Symptoms




ትኩሳት
**High Fever**



የትንፋሽ ማጠር
**Trouble Breathing**



ሳል
**Cough**

## የሚደረጉ ጥንቃቄዎች | Prevention



አለመጨባበጥ
do not shake hands




ባልታጠበ እጅ ፊትዎን አለመንካት
Avoid touching Eyes, Nose & Mouth



አፍን መሸፈን
Use face mask



እጅ በሳሙና መታጠብ
Wash your hands with soap & water



አካላዊ ርቀትን በ2 ሜትር መጠበቅ
Keep 2m distance from others

# Proverbs & Quotes

Good bankers, like good tea, can only be appreciated when they are in hot water.
**- Jaffar Hussein**

Life is a bank account, there are no withdrawals without first putting something in.
**- Ray Torres**

“Today is hard, tomorrow will be worse, but the day after tomorrow will be sunshine.”
**Jack Ma**

## አዋሽን የሆነው ማነው?

ገና ከመነሻው ግልጋሎት ሲጀምር
ታላቅ ህልም ሰንቆ ምስረታውን ሲያበስር
የሁሉም አለኝታ ድንቅ ስመ ገናና
አዋሽ ባንካችን ነው መሰረቱ የፀና
ዘመን ሲለዋወጥ አብሮ እየዘመነ
በመላ ሀገሪቱ ተደራሽ የሆነ
በውድ ደንበኞቹ ፍፁም የታመነ
ባንካችን አዋሽ ነው መከታ የሆነ
እልፍ ጥረቶቹን ወደፊት አድርጎ
የችግር መፍቻን ቁልፍ ሳይደክመው ፈልጎ
አላማን ከተግባር ሁሌ እያዋደደ
ከስር መሰረቱ ድህነትን ናደ
ማነው ባለራዕይ አዋሽን የሆነ
በመሪነት መድረክ ስራን የከወነ
ሁሉን በማስደመም እጅግ የተለየ
ከላይ ታች ቢፈለግ ከቶ መቼ ታየ
ይህው ሌላ ታሪክ የአዋሽ ብስራት ዜና
ድልን ተቀናጅቶ በስኬት ጎዳና
በፋይናንስ ዘርፉ ሁሌ እያስገረመ
በጠንካራ አለት ላይ ዝናውን አተመ

ሰላም ተክለጽዮን
ማርኬቲንግ እና ኮምዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት

ካለዎት ላይ ይቆጥቡ
ነገዎን ብሩህ
ያድርጉ







# የዓለም ቁጠባ ቀን

# WORLD SAVINGS DAY

*"When You save a bit,*
*Big things follow"*










.. መደበኛ እና ሌሎችም የቁጠባ
አማራጮች ከአዋሽ ባንክ

WORLD
SAVINGS DAY
2020
31 October

አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River